# የኢዴፓ 5ኛ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠናቀቀ

መጋቢት 11 እና 12 ቀን 2003 ዓ.ም የተካሄደው የኢዴፓ አምስተኛ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍ በዛሬው እለት ተጠናቋል፡፡ ጉባኤው በትናትናው እለት ባካሄደው ስብሰባ የፓርቲው የማእከላዊ ምክር ቤት የስራ ክንውን ሪፖርትና የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ሪፖርትን አዳምጦ አፅድቋል፡፡ በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የፓርቲው አመራር ለጉባኤው በአስር አገራዊ ጉዳዮች ላይ አቋም ወስዶል፡፡

የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተ ባደረገው ውይይትም የፓርቲው የማእከላዊ ምክርቤት ቁጥር ከ 17 ወደ 25 የፓርቲውን ስራ አመራር ቁጥር ከ 7 ወደ 9 ከፍ እንዲል ወስኗል፡፡ ይህንን የደንብ ማሻሻያ መሰረት በማድረግም ፓርቲውን ለመጪዎቹ ሁለት አመታት የሚመሩ 25 የማእከላዊ ምክር ቤት አባላትንና 9 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን መርጦል፡፡

በዛሬ እለት በራስ ሆቴል በተደረገው የመዝጊያ ስነ-ስርአት ጉባኤው አቋም የወሰደባቸው አገራዊ ጉዳዮች ይፋ የተደረጉ ሲሆን እስካሁን በስራ ላይ የነበሩት እና የስራ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁት አቶ ልደቱ አያሌው ለተተኪው የፓርቲ መሪ ለአቶ ሙሼ ሰሙ ሀላፊነታቸውን በይፋ አስረክበዋል፡፡ ፓርቲውን ለመጪው ሁለት አመታት እንዲመሩ የተመረጡት የስራ አመራር አባላትም ለህዝብ ይፋ ተደርገዋል፡፡

# የኢዴፓ 5ኛ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ተወያይቶ አቋም የወሰደባቸው አገራዊ አጀዳዎች

## 1. የሊበራል ዴሞክራሲ አዋጭነት በኢትዮጵያ

ጉባዔው በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ባደረገው ጥልቅ ውይይት - የሊበራል ዴሞክራሲ ታሪካዊ አመጣጥንና በአሁኑ ወቅት የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ፤ ሊበራል ዴሞክራሲ ከሌሎች ርዕዮተአለማዊ አቅጣጫዎች ጋር ሲነጻጸር ዘላቂ ሰላምን ከማምጣት፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ከማጠናከር፣ ማህበራዊ ችግሮችን ከማቃለል፣ የመቻቻል ፖለቲካን ከማስፈን፣ በእውነተኛ የነፃ-ገበያ ስርአት አማካኝነት ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን ከማምጣትና የግልንና የቡድን መብቶችን በተሟላ ሁኔታ ከማክበር አንፃር ያለውን ጠቀሜታ ተወያይቶበታል፡፡ በአጠቃላይም ሊበራል ዴሞክራሲ በአሁኑ ወቅት ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ከሚያራምደው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር በተነፃፃሪ የአገራችንን ወቅታዊ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት ተመራጭ የሚያደርጉትን ባህሪዎች ለመገምገም ሞክሮል፡፡

ሊበራሊዝም ከብዙ መቶ አመታት ጀምሮ በምዕራቡ ዓለም ባሳለፈው ሂደት ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እራሱን እያጣጣመ፣ ከራሱ ድክመቶችና ስህተቶች በድፍረት እየተማረና በሌሎች ርዕዮተ-ዓለማዊ መስመሮች ውስጥ ያሉ በጎና ጠቃሚ አስተሳሰቦችን ጭምር በሂደት እየተቀበለ እራሱን በስክነት በማደስና በማጠናከር በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ ከሁሉም የተሻለ ገዢ አስተሳሰብ ለመሆን የበቃ መስመር መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ሊብራሊዝም በአንድ በኩል ሁሉም ነገር እንደነበረ ይቀጥል የሚል አክራሪነትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ነገር ስር ነቀል በሆነ የህዝብ እንቅስቃሴ በዘመቻ መልክ ይለወጥ የሚል የአብዮታዊነት ባህሪን የሚቃወምና በጥናትና በህብረተሰብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ የሰከነ ለውጥን የሚደግፍ መስመር በመሆኑ በሃገራችን ዘላቂ ሰላምና የመቻቻል ፖለቲካ እንዲመጣ የሚያስችል መስመር መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሊበራል ዴሞክራሲ በአንድ አገር ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊመጣ የሚችለው በመንግስት ሳይሆን በዋናነት በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የማይተካ ሚና ነው ብሎ የሚያምን መስመር በመሆኑ በአገራችን እውነተኛ የነፃ-ገበያ ስርዓት እንዲጠናከርም ሆነ ስራ ፈጣሪ የሆነ የኢንቨስትመንት መስክ በበቂ መጠን እንዲስፋፋ የተሻለ አማራጭ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ሊበራል ዴሞክራሲ አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ በህዝብ ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ማህበራዊ ቀውሶችን ለመታደግ ሲባል በኢኮኖሚ ውስጥ የሚደረግን በህግ የተገደበ የመንግስት ጣልቃ ገብነትና ጊዜያዊ የድጎማ አሰራሮችን የሚደግፍ በመሆኑም "ሊበራሊዝም ለሃብታሞች ብቻ የቆመ ስርአት ነው" በሚል ከአንዳድ የግራ ኃይሎች የሚቀርብበትን ትችት ጊዜው ያለፈበትና ሊብራሊዝም በአሁኑ ወቅት የደረሰበትን ደረጃ በአግባቡ ያላገናዘበ ትችት እንደሚያደርገው ታምኖበታል።

ሊበራሊዝም የሁሉንም ዜጎች መብት በእኩልነትና በተሟላ ሁኔታ ለማክበር ለሚያስችለው የግለሰቦች መብት መከበር ቀዳሚና ልዩ ትኩረት የሚሰጥ አስተሣሠብ በመሆኑ ዜጎች ከየግል አስተሣሠባቸውና ፍላጎታቸው በመነጨ እንዲከበርላቸው የሚፈልጉት የቡድን መብትም በተሟላ ሁኔታ ሊከበር የሚችለው በሊበራል ዴሞክራሲ አስተሣሠብ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ጉባዔው ከዚህ አጠቃላይ ግምገማ በመነሳትና ኢዴፓ ቀደም ሲል ባካሄዳቸው ድርጅታዊ ጉባኤዎቹ ሊበራል ዴሞክራሲን ለማራመድ የወሰናቸው ውሳኔዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በማመን ሊበራል ዴሞክራሲ የፓርቲው ርዕዮተ ዓለማዊ መስመር ሆኖ እንዲቀጥል የወሰነ ሲሆን ከዚህ አቋሙ ጋር በተያያዘም ኢዴፓ ከርዕዮተ-ዓለም አሰላለፍ አንፃር የሚኖረው ቦታ አሁንም መካከለኛ ቀኝ (center right) ሆኖ እንደሚቀጥል አምኖበታል፡፡

## 2. ሕገ-መንግስት

ጉባዔው የወቅቱን የአገሪቱን ሕገ-መንግስት በተመለከተ ባደረገው አጠቃላይ ውይይት አሁን በሥራ ላይ ያለው የአገራችን ሕገ-መንግስት በተረቀቀበትና በፀደቀበት ወቅት ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የራሱ ድርጅታዊ የፖለቲካ አቋሞች በሕገ-መንግስቱ ውስጥ እንዲካተቱና ከአግባብ በላይ የሆነ የበላይነት እንዲያገኙ እንዳደረገ፤ ሕገ-መንግሥቱን በማርቀቁና በማፅደቁ ሂደትም ሌሎች የተለየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች በቂ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እንዳልተደረገ፤ እነዚህን ምክንያቶች ሰበብ በማድረግም አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህገ-መንግስቱን ሙሉ ለሙሉ እውቅና ወደ መንፈግ ተገቢ ያልሆነ አክራሪ አቋም እንደገቡና በእነዚህ መሰረታዊ ምክንያቶችም የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች በአገሪቱ የወቅቱ ሕገ-መንግስት ዙሪያ ብሄራዊ መግባባት መፍጠር እንዳልቻሉ አምኖበታል፡፡ በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት ካልፈጠሩ በስተቀር የተረጋጋና ዘላቂ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ሊፈጠር እንደማይችል የተገነዘበው የኢዴፓ ጉባዔ- በአንድ በኩል ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ከወቅቱ የአገሪቱ ሕገ-መንግስት መንፈስ በሚቃረን ሁኔታ ሕገ-መንግስቱን ምንም አይነት ጥያቄ ሊነሳበት የማይገባ ኃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) ሰነድ አድርጐ በማየት ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ያለምንም ቅሬታና ጥያቄ ሙሉ በሙሉ እንዲያምኑበት የሚፈልግ መሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሕገ-መንግስቱ ተገቢውን እውቅናና አክብሮት ባለመስጠት በሂደት በሕዝብ ውሳኔ እንዲሻሻል ከመታገል ይልቅ እንደ አንድ ተራ ሰነድ ተቀዶ እንዲጣል የሚጠይቅ አክራሪ አቋም የሚያራምዱ መሆናቸው በሕገ-መንግስቱ ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዳይፈጠር እንቅፋት መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ጉባዔው ርዕሰ-ጉዳዩን አስመልክቶ ባደረገው ውይይት የወቅቱን ሕገ-መንግስት በተመለከተ ገዥው ፓርቲም ሆነ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያራምዱት አቋም መሰረታዊ ችግር እንዳለበት አምኖበታል፡፡ የማንኛውም አገር ሕገ-መንግስት በአንድ ወቅታዊ ሁኔታ ፀድቆ በሂደት ከህብረተሰቡ የእድገት ደረጃና የፖለቲካ ሁኔታ አንፃር እየተሻሻለ የሚሄድ ሰነድ መሆኑ እየታወቀና ማንኛውም ሕገ-መንግስት እንዴት ሊሻሻል እንደሚችል እራሱን የቻለ የማሻሻያ አንቀፅ አካቶ የሚቀረፀውም በዚሁ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ ኢህአዴግ ሁልጊዜ ሕገ-መንግስቱ ምንም አይነት ትችትና ተቃውሞ ሊነሳበት የማይችል ዘላለማዊ ሰነድ እንደሆነ አድርጐ በማሰብ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ የሚያቀርበው ትችት የተሳሳተና ከራሱ ከሕገ-መንግሥቱ መንፈስ የሚቃረን መሆኑን አምኖበታል፡፡ ጉባዔው በዴሞክራሲያዊ ይዘቱ እንደ አንድ በጐ ምሳሌ የሚጠቀሰው የአሜሪካን ሕገ-መንግስት በውስጡ ከአገሪቱና ከህዝቡ የእድገት ደረጃ ጋር አብረው የማይሄዱ ድንጋጌዎች ያሉት መሆኑ በሂደት እየታወቀ ሲመጣ ለ 27 ጊዜ እንዲሻሻል የተደረገ መሆኑን በማስታወስም ኢህአዴግ በአገራችን የሕገ-መንግስት ማሻሻያ የሚጠይቁ ፓርቲዎችን እንደ ፀረ-ዴሞክራሲና ሕገ-ወጥ አካል መቁጠሩ ስህተት መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ኢህአዴግ እንደ ገዥ ፓርቲነቱ የአገሪቱ ሕገ-መንግስት በአግባቡ እንዲከበርና የበላይ ሕግ ሆኖ አገሪቱን እንዲያስተዳድር የማድረግ ኃለፊነት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ህገ-መንግስቱ ምንም አይነት ተቃውሞና ትችት እንዳይቀርብበት መጠበቁ ግን የተሳሳተና ከራሱ ከሕገ-መንግስቱ መንፈስ ጋር የሚቃረን አመለካከት መሆኑ ተሰምሮበታል፡፡ የኢትዮጵያ የወቅቱ ሕገ-መንግስት ዜጎች ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ማንኛውንም ጉዳይ የመቃወም መብት ያላቸው መሆኑን እውቅና የሰጠ ስለሆነ እራሱን ሕገ-መንግስቱን መቃወምም ከራሱ ከሕገ-መንግስቱ የሚመነጭ መብት መሆኑን ኢህአዴግ አምኖ መቀበል እንዳለበት ጉባዔው አምኖበታል፡፡

ጉባዔው አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህገ-መንግሥቱን በተመለከተ የሚያራምዱትን አቋም ለመገምገም ባደረገው ሙከራም በአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሕግ እውቅና አግኝተው መንቀሳቀስ የቻሉትና ወደፊትም ሕጋዊ ዋስትና ሊኖራቸው የሚችለው በስራ ላይ የሚገኘው ሕገ-መንግስት እውቅና የሰጣቸው ፖለቲካዊና ሰብአዊ መብቶች ሲከበሩ ስለሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕገ-መንግቱን የማክበርና በሕገ-መንግስቱ የመገዛት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን አምኖበታል፡፡ ጉባዔው በአንድ አገር አንድ ሕግ መከበር ያለበት ሕጉ “ጥሩ” ወይም “ትክክለኛ” ነው

ተብሎ ስለታመነ ብቻ ሳይሆን ሕጉ የአገሪቱ ሕግ ሆኖ በስራ ላይ እስካለ ድረስ በማንኛውም ዜጋም ሆነ የፖለቲካ ኃይል መከበር ስላለበት መሆኑን አፅንኦት ሰጥቶ ተወያይቶበታል። አንድ ሕግ የፀደቀበትን ትክክለኛ ያልሆነ ሂደትም ሆነ በውስጡ የሚገኙ መሻሻል ይገባቸዋል ተብለው የሚታመኑ አንቀፆችን ምክንያት በማድረግ ሕጉን አለማክበርና በሕጉ አለመገዛት ስለማይቻል አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዚህ እረገድ የሚያራምዱት የተሳሳተ አቋም መስተካከል እንዳለበትና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕገ-መንግስቱን ማክበር ብቻም ሳይሆን የማስከበር ኃላፊነትም ያለባቸው መሆኑን አምነው መቀበል እንዳለባቸው አምኖበታል፡፡

አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለወቅቱ የአገሪቱ ሕገ-መንግስት ተገቢ እውቅና ባለመስጠት የሚያራምዱት አክራሪ አቋምም ገዥው ፓርቲ እራሱን እንደ ሕግ አስከባሪ፣ ተቃዋሚዎችን ደግሞ እንደ ሕገ-ወጥ ኃይሎች አድርጐ በማቅረብ ያልተገባ የፕሮፓጋንዳ ጥቅም እንዲያገኝ እንደረዳው ታምኖበታል፡፡ ስለሆነም ኢዴፓ በአንድ በኩል በወቅቱ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የሚገኙ ለአገሪቱ አንድነትና የኢኮኖሚ እድገት እንቅፋት የሆኑ አንቀፆች እራሱ ሕገ-መንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት በሕዝብ ውሳኔ እንዲሻሻሉ የሚያደርገውን ትግል የበለጠ አጠናክሮ እንዲቀጥል፤ በተመሳሳይ ሁኔታም ኢዴፓ ሕገ-መንግስቱን ማክበርና በሕገ-መንግስቱ መገዛት ብቻም ሳይሆን ሌሎች የአገሪቱ ዜጎችም ሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች ሕገ-መንግስቱን በተመሳሳይ ሁኔታ የማክበርና በሕገ-መንግስቱ የመገዛት ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ግልፅ አቋም ወስዶ መታገልና ማስተማር እንዳለበት ጉባዔው አምኖበታል፡፡

የአገሪቱን ሕገ-መንግስት አፈፃፀም በተመለከተ ጉባዔው ባደረገው ግምገማም በአንድ በኩል በተለያዩ ጊዜያት ገዥው ፓርቲ የሚያወጣቸው አዋጆችና መመሪያዎች ከሕገ-መንግስቱ መንፈስ በሚቃረን ሁኔታ የሕግ-አውጪውንና የሕግ-ተርጓሚውን ኃላፊነትና ስልጣን ለአስፈፃሚው አካል የሚሰጡ በመሆናቸው፤ በሌላ በኩል በሕገ-መንግስቱ እውቅና ያገኙ የዜጎች ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶችም በአስፈፃሚው አካል በየእለቱ በሰፊው የሚጣሱበት ሁኔታ በአገራችን እየታየ በመሆኑ ኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ያላት አገር ብትሆንም ሕገ-መንግስታዊነት የሰፈነባት አገር ለመሆን ግን ገና እንዳልቻለች ታምኖበታል፡፡ ኢህአዴግ ሁልጊዜ ሕገ-መንግስቱን ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችና ዜጐች እንዲያከብሩትና እንዲገዙበት ሲወተውት የሚደመጥ ቢሆንም ከማንም በላይ ግን እራሱ በተግባር ሕገ-መንግስቱን አክብሮ መገኘት የተሳነው እራሱ ገዢው ፓርቲ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

የአገሪቱን ህገ-መንግስት በተመለከተ ያለውን አጠቃላይ አቋም በዚህ መልኩ ያስቀመጠው የኢዴፓ ጉባኤ ዋና ዋና በሚባሉ ህገ-መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ የሚከተሉትን አቋሞች ወስዷል፡፡

## 3. ህገ-መንግስታዊ ጉዳዮች

### 3.1. የአገር ባለቤትነት ጉዳይ

የወቅቱን የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ቀደም ሲል በስራ ላይ ከነበሩት የአገሪቱ ህገ-መንግስቶችም ሆነ ከሌሎች አገሮች ህገ-መንግስቶች በዋናነት የተለየ የሚያደርገው የአገሪቱን ባለቤትነት ለእያንዳንዱ የአገሪቱ ዜጐች ሳይሆን ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ለሚባሉ ቡድኖች የሰጠ መሆኑ ነው፡፡ በ 1985 ዓ.ም የፀደቀው የወቅቱ የአገሪቱ ህገ-መንግስት ኢትዮጵያን እንደ አንድ ነባር አገር ሳይሆን በብሄር ብሄረሰቦች ድርድርና ስምምነት እንደተፈጠረች አዲስ አገር የሚቆጥር ነው፡፡ ለአገሪቱ አንድነትና የወደፊት ህልውና አደጋ የሚሆኑ አንቀፅ 39 ን የመሳሰሉ የተለያዩ አንቀፆች በህገ-መንግስቱ ውስጥ እንዲካተቱ የተደረገውም ከዚሁ የአገሪቱን ባለቤትነት ከዜጐች እጅ አውጥቶ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ለሚባሉ ቡድኖች ከመስጠቱ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ የአንድ አገር የባለቤትነት መብት የራሳቸውን ማንነት በብሄረሰባዊ ማንነታቸው ለሚገልፁ ዜጐች ብቻ ሳይሆን እራሳቸውን በሌሎች በተለያዩ የማንነት መገለጫዎች ለሚገልፁ የአገሪቱ ዜጐች ጭምር ያለ ልዩነት መሰጠት ያለበት መብት ስለሆነ የወቅቱ የአገሪቱ ህገ-መንግስት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የአገሪቱ ባለቤት እንዲሆን በሚያስችል ሁኔታ መሻሻል እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

### 3.2 የፌደራል አደረጃጀት

የወቅቱ የአገሪቱ ሕገ-መንግስት የአገሪቱ ባለቤቶች ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሆኑ ከማድረጉ ጋር በተያያዘ የአገሪቱ የፌደራል አደረጃጀትም በዋናነት ቋንቋንና ብሄረሰባዊ ማንነትን መሰረት አድርጐ የተደራጀ ነው፡፡ ከታሪካዊ አመጣጡም ሆነ በሌሎች ጥቅም ላይ በዋለባቸው አገሮች እንደሚታየው የፌደራሊዝም ዋና ጥቅም

በአንድ አገር ተገቢ የሆነ የስልጣን ክፍፍልንና ቁጥጥርን ማስፈን፣ የፖለቲካ ስልጣንን ወደታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ማዳረስንና ፍትሃዊ የሐብት ክፍፍልንና የልማት ስርጭትን ማምጣት ነው፡፡ በእኛ አገር ግን የፌደራል አደረጃጀት በዋናነት ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው አገሪቱ ካሉባት በርካታ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ውስጥ አንዱ የሆነውን የብሄር ጥያቄን ለመፍታት ተብሎ ነው፡፡ ጉባዔው ባደረገው ውይይት የአገሪቱ የፌደራል አደረጃጀት የብሄር ጥያቄን ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ከድህነት የመላቀቅ የልማት ጥያቄ፣ የመልካም አስተዳደር ጥያቄንና የህዝቡን በእኩልነት በአንድነት አብሮ የመኖር ጥያቄ ለመመለስ በሚያስችል መልኩ መደራጀት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ ስለሆነም አሁን በስራ ላይ የዋለውና በዋናነት ቋንቋንና ብሄረሰባዊ ማንነትን መሰረት አድርጎ የተዋቀረው የፌደራል ስርዓት የአገሪቱን የመሬት አቀማመጥ፣ የህዝብ ብዛትን፣ የህዝቡን አብሮ የመኖር ታሪካዊ ትስስር፣ የአስተዳደር አመችነትን፣የኃብት ክፍፍልንና የልማት እድገት መመጣጠንን፣ ቋንቋንና ብረሰብዓዊ ማንነትን እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በተናጠልና በጋራ ባገናዘበ መልኩ በህዝብ ብዛታቸውና በቆዳ ስፋታቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ክልላዊ መስተዳድሮችን በአገሪቱ ለመፍጠር በሚያስችል ሁኔታ እንደገና መዋቀር እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡

### 3.3. የመገንጠል ጥያቄ

በወቅቱ የአገሪቱ ህገ-መንግስት የአገሪቱ ባለቤቶች ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሆኑ ከመደረጉ ጋር ተያይዞ እነዚህ የአገሪቱ ባለቤቶች በፈለጉ ጊዜ ከአገሪቱ የመገንጠል መብት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 39 አማካኝነት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከሌሎች ህገ-መንግስታዊ ጉዳዮች በተለየ ይህ በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ በኢትዮጵያ ብቻ እንዲኖር የተደረገው የመገንጠል መብት በህገ-መንግስቱ ውስጥ ለብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሰጥ የተደረገው ያለምንም ገደብ ሲሆን አንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ለመገንጠል ሲፈልግም የመገንጠሉን ውሳኔ ከራሱ ውጭ ሌላ አካል እንዲመረምረውም ሆነ እንዲጋራው አልተደረገም፡፡ አንዳንድ የአገሪቱ ክልሎች የመገንጠል ጥያቄ ቢያነሱና በህገ-መንግስቱ መሰረት የመገንጠል ጥያቄው ተግባራዊ እንዲሆን ቢደረግ ውጤቱ "ኢትዮጵያ" በመባል የምትታወቀውን አገር ህልውና የሚያፈርስ መሆኑ እየታወቀም እንዲህ ዓይነቱን ከአገር ህልውና ጋር የተያያዘ አደጋ ለማስቀረት የሚያስችል መፍትሄ በህገ-መንግስቱ ውስጥ አልተቀመጠም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጉባዔው ባደረገው ውይይት የአንድ አገር ህገ-መንግስት በዋናነት ማተኮር ያለበት በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተፈተው የህዝብና የአገር አንድነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ በመሆኑ የወቅቱ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስትም ከአገሪቱ የወደፊት አንድነትና ህልውና ጋር በተያያዘ ሊሻሻል እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡ስለሆነም የመገንጠልን መብት ያለምንም ገደብ ለብሄር ብሄረሰቦች የሰጠው አንቀፅ 39 የአገሪቱን ህልውና የሚፈታተንና በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ የሚችል አደጋ በውስጡ የያዘ መሆኑ ታውቆ በህዝብ ውሳኔ ሊሻሻል እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡

### 3.4. የሃብት ክፍፍልና የመሬት ጥያቄ

የፌደራል አደረጃጀት በአንድ አገር ተግባራዊ እንዲሆን ከሚያስፈልግባቸው ምክንያቶች አንዱ ተመጣጣኝ የሃብት ክፍፍልና የልማት ስርጭትን ለማምጣት ቢሆንም በዚህ ረገድ የወቅቱ የአገሪቱ ህገ-መንግስት ድክመት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ እውነተኛ የፌደራል አደረጃጀት ፖለቲካዊ መብቶችን ብቻ ሳይሆን ትርጉም ያላቸው ኢኮኖሚያዊ መብቶችን ጭምር ለክልል አስተዳደሮች በመስጠት የሚገለፅ ቢሆንም የወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግስት ትርጉም ያለው የኢኮኖሚያዊ መብት ለክልሎች አልሰጣቸውም፡፡ በወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግስት ዋና ዋና የሚባሉ የገቢ ርዕሶችን የራሱ በማድረግ ከ 90% በላይ የሆነውን የአገሪቱን የገንዘብ ገቢ የሚሰበስበው የፌደራል መንግስቱ ሲሆን በዚህም ምክንያት ክልሎች የሚተዳደሩት እራሳቸው በሚሰበስቡት ገቢ ሳይሆን በዋናነት ከፌደራል መንግስቱ በሚደረግላቸው ድጎማ ነው፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን በሚመለከት ክልሎች የተሰጣቸው መብት የፌደራል መንግስቱ በሚያወጣው ህግ መሰረት የማስተዳደር ነው እንጂ የተፈጥሮ ሃብትን በባለቤትነት የመያዝም ሆነ እንደየ አካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ የተፈጥሮ ኃብትን በተመለከተ የራሳቸውን ህግ አውጥተው የመጠቀም መብት የላቸውም፡፡ እንዲህ አይነቱ አሰራር የአገሪቱን ፌደራሊዝም እውነተኛ ፌደራሊዝም ሊያደርገው ስለማይችል ክልሎች ገቢ በመሰብሰብና የተፈጥሮ ሃብትን በባለቤትነት ይዞ በመጠቀም ረገድ የተሻለና ትርጉም ያለው መብት እንዲኖራቸው በሚያደርግ መጠን ህገ-መንግስቱ መሻሻል እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ በአገራችን ዋና የተፈጥሮ ሃብትና የሃብት ምንጭ የሆነው መሬትም እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በግል፣በጋራና በመንግስት ይዞታ ስር ሆኖ የአገሪቱን ዕድገት በሚያፋጥን ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋል ስላለበት "መሬት የመንግስት ነው" የሚለው የአገራችን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ መሻሻል እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

## 3.5. የፌደሬሽን ምክር ቤት ሚና

በወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግስት የፌዴሬሽን ምክርቤት የተሰጠው ስልጣን ህግ የማውጣት ሳይሆን ህገ-መንግስት የመተርጐም ነው፡፡ የምክር ቤቱ አባላትም በህዝብ ቀጥተኛ ምርጫ ተመርጠው የሚወከሉ ሳይሆን ከክልል ምክር ቤቶች ተመርጠው የሚላኩና የላካቸውን የክልል ምክር ቤት ሳይሆን በአገሪቱ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦችን ወክለው የሚወስኑ ናቸው፡፡ ይህ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አሰራርና አወቃቀር በርካታ ድክመቶች ያሉበት መሆኑ ታምኖበታል፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የፖለቲካ ሰዎች ስብስብ ሆኖ እያለ ህገ-መንግስትን የመተርጐም የዳኝነት ስራ እንዲሰራ መደረጉ በሌሎች አገሮች ያልተለመደና ተገቢ ያልሆነ አሰራር መሆኑ የታመነበት ሲሆን በሌሎች አገሮች እንደሚገኙ ሴኔቶች ክልሎች በእኩል መጠን የሚወከሉበት ምክር ቤት መሆን ሲገባው ብሄር ብሄረሰቦች እንዲወከሉበት መደረጉም ተገቢ አለመሆኑ ታምኖበታል፡፡ እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት በውስጡ በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች የሚገኙበት አንድ ክልል ብቻውን ከሌሎች የአገሪቱ ስምንት ክልሎች የበለጠ ድምፅ በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲኖረው በማድረግም ከተመጣጣኝ ውክልናም ሆነ ከዴሞክራሲያዊ የውሳኔ አሰጣጥ ጋር የማይሄድ አሠራር መፍጠሩ ታምኖበታል፡፡ ስለሆነም የአገሪቱ የፌደሬሽን ምክር ቤት በህዝብ ቀጥተኛ ምርጫ ተመርጠው ክልሎችን በእኩልነት መጠን የሚወከሉ አባላት የሚገኙበት ምክር ቤት እንዲሆን፣ ኃላፊነቱም ህገ-መንግስት የመተርጐም ሳይሆን ህግ የማውጣት እንዲሆን በሚያስችል መልኩ መሻሻል እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

## 3.6. የምርጫ ስርአት

የወቅት የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የአገሪቱ የምርጫ ስርአት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የኢትዮጵያ የምርጫ ስርአት በየምርጫ ክልሉ ለምርጫ ውድድር ከቀረቡ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ውስጥ የተሻለ አብላጫ ድምፅ ያገኘው ፓርቲ አሸናፊ እንዲሆን የሚያደርግ (first past the post) ስርአት ነው፡፡ ይህ አይነቱ የምርጫ ስርአት ከፍተኛ የህዝብ ድምፅ እንዲባክን የሚያደርግና የአናሳዎች ድምፅ ቢያንስ የመደመጥ ውክልና እንዳያገኝ የሚያደርግ በመሆኑ፤ አንዳንድ ጊዜም አብዛኛው ህዝብ የአናሳ ውክልና ባላቸው የፖለቲካ ሃይሎች እንዲገዛ የሚያደርግ ውጤት የሚያስከትል የምርጫ ስርአት በመሆኑ ሊሻሻል እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡ በአገራችን እስካሁን በተካሄዱ ምርጫዎች (በተለይም በምርጫ 2002) ይህ የምርጫ ስርአት የብዙሃን ፓርቲ አሠራርን በሂደት እያቀጨጨ መምጣቱ በተግባር የተረጋገጠ በመሆኑ የአገራችን የምርጫ ስርአት ከአብላጫ ድምፅ አሸናፊነት ይልቅ ወደ ተመጣጣኝ የውክልና ስርአት (proportional representation) መለወጥ እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

## 3.7. ሕገ-መንግሥት ስለማሻሻል

በወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግስት የመገንጠል መብትን የመሰሉ ከአገሪቱ ህልውና ጋር የተያያዙ አሳሳቢ ጉዳዮች በቀላሉ የሚወሰኑበት አሰራር የተቀመጠ ቢሆንም በአጠቃላይ ህገ-መንግስቱን የማሻሻል ጉዳይ ግን “የማይቻል” በሚባል መጠን በጥብቅ የታሰረ ሆኖ እናገኘዋለን። በአሁኑ ወቅት የህገ-መንግስት ማሻሻያ ሃሳብ ለማመንጨት የተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤት በ 2/3 ኛ ድምፅ፣ ከክልል ምክር ቤቶች ውስጥ ደግሞ አንድ ሶስተኛው በድምፅ ብልጫ መደገፍ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ ህገ-መንግስቱን ለማሻሻል (በተለይም ምዕራፍ ሶስትን ሙሉ በሙሉና አንቀፅ 104 እና 105 ን ለማሻሻል) የህዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤት በ 2/3 ኛ ድምፅና ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በአብላጫ ድምፅ ሊደግፉት ይገባል። ይህም ማለት ከአገሪቱ ዘጠኝ ክልሎች ውስጥ አንድ በህዝብ ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ ክልል ብቻውን የሚቃወመው ማንኛውም የህገመንግስት ማሻሻያ ሃሳብ ተቀባይነት አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰራር ህገ-መንግስቱ በሂደት ሊሻሻል የሚገባው የፖለቲካ ሰነድ መሆኑን የረሣና በአገሪቱ ወደፊት ፈፅሞ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ማድረግ የማያስችል ግትር (rigid) ድንጋጌ በመሆኑ ሊሻሻል እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡

ጉባዔው በጉዳዩ ላይ ባደረገው ውይይት የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ሃሳብ ለማመንጨት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌደሬሽን ምክር ቤት በአብላጫ ድምፅ መወሰናቸው የሚበቃ ሲሆን፣ ህገ-መንግስቱን ለማሻሻል ደግሞ የህዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤት 2/3 ኛ ድምፅ በቂ መሆን እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት ክልሎች በእኩልነት የሚወከሉበት ምክር ቤት እንዲሆን ከተደረገ በፌደሬሽን ምክር ቤት 2/3 ኛ ድምጽ የሚወሰን ማናቸውም ውሣኔ በተዘዋዋሪ በክልሎች 2/3 ኛ ድምጽ የደገፈ መሆኑ ስለማይቀር ከዚህበ ላይ በተጠቀሰው ቀመር መሰረት ህገ-መንግስቱን የማሻሻል አሰራር ቢቀመጥ አሰራሩ የአብዛኛውን ክልሎች ውሣኔ

መሠረት አድርጐ የሚፈጸም እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡ የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ አንቀጽ በአንድ ሕገ-መንግሥት ውስጥ ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑም ይህ የህገ-መንግስቱን ማሻሸያ አንቀጽ ለማሻሻል የሚያስችል ውሳኔ መስጠት ያለበት በሕዝበ ውሳኔ (referendum) መሆን እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡

## 4. ማህበራዊ ጉዳዮች

ማህበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በዋናነት ጉባዔው ውይይት ያደረገባቸው ትምህርትና ጤና ሲሆኑ የሴቶች፣ የወጣቶች፣የህፃናትና የአካል ጉዳተኞች ጉዳዮችም ትኩረት የሚያሻቸው ማህበራዊ ጉዳዮች መሆናቸው ታምኖባቸው ውይይት ተደርጐባቸዋል፡፡

ትምህርትን በተመለከተ በተደረገው ውይይት በአሁኑ ወቅት መንግስት በትምህርት ተደራሽነት ረገድ የሚያስመሰግን ስራ እየሰራ እንደሆነ የታመነበት ሲሆን የትምህርት ጥራትን በተመለከተ የሚታየው ችግር ግን እጅግ ሰፊና አሳሳቢ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ አንድን ትውልድ ለአገርና ለወገን በሚጠቅም መልኩ በመቅረፅ እረገድ የትምህርት ሚና የማይተካና ከሁሉም በላይ በመሆኑ በዋናነት ከካሪኩለም ቀረፃ፣ ከትምህርት መርጃ መሳሪያ አቅርቦትና ከመምህራን ብቃትና ብዛት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመፍታት የትምህርት ጥራትን በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት ማሻሻል እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ገዢው ፓርቲ መምህራንንና ተማሪዎችን የራሱ የፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ በማሰብ በትምህርት ተቋማት ዙሪያ የሚፈፅመው መጠነ ሰፊ ድርጅታዊ ጣልቃ ገብነት ለትምህርት ጥራት መጓደል አንድ አሳሳቢ ችግር በመሆኑ ሊወገድ እንደሚገባው ታምኖበታል፡፡

ጤናን በተመለከተ በተደረገው ውይይት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የጤና ተቋማትን በማዳረስ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስንና ወባን በመከላከል ረገድ መንግስት አበረታች ተግባር እያከናወነ መሆኑ የታመነበት ሲሆን ከጥራት አኳያ ግን ከጤና መርጃ መሳሪያዎች፣ ከመድሃኒትና ከጤና ባለሙያዎች እጥረት ጋር በተያያዘ በጤናውም ዙሪያ ከፍተኛ ድክመት እንደሚታይ ታምኖበታል፡፡ በከተሞች አካባቢ የጤና ጉዳይ በቂ ትኩረት ያላገኘ ከመሆኑም በላይ በከተሞች አካባቢ እየተስፋፉ የሚገኙት በዋናነት የግል የጤና ተቋማት በመሆናቸው ከህዝቡ አቅም ጋር በማይመጣጠን ደረጃ የህክምና ዋጋ ውድ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጤናው ሴክተር ዙሪያ የሚታየው የጤና ባለሙያዎች የስነምግባር ጉድለት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ በመሆኑ አስቸኳይ መፍትሄ እንደሚያስፈልገው ታምኖበታል፡፡

ከትምህርትና ከጤና ጉዳይ በተጨማሪ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በተደረገው ውይይት የህብረተሰቡ ግማሽ አካል ለሆኑት ሴቶች የሚሰጠው ትኩረት ከፕሮፓጋንዳና ከድርጅታዊ የፖለቲካ ጥቅም በፀዳ አኳኋን ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፤ የእናቶችና የህፃናት ሞትን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው፤ በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠሩ የአገራችን አካል ጉዳተኞች በዙሪያቸው የሚታዩ ፈርጀ ብዙ ችግሮች እንዲፈቱ የሚያስችል ጥረት መደረግ እንዳለበት፤ የአገሪቱ ተረካቢ የሆኑትን ወጣቶች በተመለከተ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን በማሟላት ረገድ ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ጥረትና እርብርብ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል፡፡

## 5. ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች

ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በተደረገው ውይይት በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው ጥያቄዎች-በአገሪቱ የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስት ሚና እስከምን ድረስ ሊሆን ይገባል?፤ አገሪቱ ልትከተለው የሚገባው የኢኮኖሚ ስትራቴጂስ ምን ዓይነት ሊሆን ይገባል? የሚሉት ጥያቄዎች ሲሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያላቸው የንግድ ድርጅቶችና የወቅቱ የኑሮ ውድነት ጉዳይም ውይይት ተደርጐባቸዋል፡፡ በውይይቱ ወቅት በአንድ በኩል ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስት ሚና የበለጠ እንዲጠናከር እየሰራ ከመሆኑና የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ገና በጥርጣሬና በስጋት የሚያይ ከመሆኑ አንፃር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ወቅት ገበያ በማረጋጋት ሰበብ በበርካታ የፍጆታ ምርቶችና ሸቀጦች ላይ እየጣለ ከሚገኘው የዋጋ ተመን አንፃር በአሁኑ ወቅት በአገራችን የዕዝ ወይም የቅይጥ ኢኮኖሚ እንጅ የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ አለ ሊባል እንደማይችል ታምበታል፡፡

በነፃ-ገበያ ስርዓት የመንግስት ዋና ተግባር ህግ የማውጣትና የገበያ ስርአቱ በአግባቡ እየተካሄደ ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ሲሆን መንግስት በህግ በተገደበ አግባብና በጊዜያዊነት በገበያ ውስጥ ተሳትፎ ሊኖረው የሚችለውም የህብረተሰቡን ጥቅም የሚጐዳ ወቅታዊ ችግር ሲፈጠርና በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊሸፈኑ ያልቻሉ ክፍተቶች ሲፈጠሩ ብቻ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ ከዚህ አንፃር መንግስት በአሁኑ ወቅት በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊሸፈኑ የሚችሉ አንዳንድ የንግድ ተቋማትን በልማት ድርጅት ስም ይዞ መቀጠሉ ተገቢ አለመሆኑ የታመነበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በንግድ ስራ ውስጥ ሊሰማራ እንደማይችል ከሚከለክለው የአገሪቱ ህግ በተፃፃሪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የበርካታ የንግድ ድርጅቶች ባለቤት ሆኖ መቀጠሉ ከነፃ-ገበያ ስርአት ጋር የሚጋጭ ስህተት ብቻም ሳይሆን በአገሪቱ ህግ መሰረት ወንጀል መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ከኢኮኖሚ ስትራቴጂ አንፃር ኢህአዴግ የሚከተለው ግብርና መር ወይም ገጠርንና አርሶ አደርን መአከል ያደረገው ስትራቴጂ በአገራችን እንዳልሰራ የኢህአዴግ የመጀመሪያዎቹ 13 የአገዛዝ ዓመታት በበቂ ሁኔታ እንዳረጋገጡ ታምኖበታል፡፡ ለአለፉት 6 ዓመታት የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት በአገራችን መታየት የቻለው ኢህአዴግ በአዋጅና በግልፅም ባይሆን ለአለፉት ስድስት ዓመታት ለኢንዱስትሪና ለአገልግሎት ዘርፉ፣ በተለይም ለከተሞችና ለኮንስትራክሽን ዘርፍ በተወሰነ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ኢህአዴግ የተቃዋሚዎችን አማራጭ ሃሳብ ተቀብዬ ተለውጫለው ማለት አሳፍሮት የቀድሞ አቋሙን ከሙሉ ልብ ለመለወጥ ባለመቻሉ እንጂ በአገሪቱ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ መሪና ተመሪ ሆነው ሳይሆን ሁሉም ዘርፎች ተገቢ ትኩረት አግኝተው እርስ በእርስ ተደጋግፈውና ተመጋግበው እንዲያድጉ የሚያስችል የኢኮኖሚ ስትራቴጂ በሙሉ ልብ ተግባራዊ ቢደረግ በአገራችን የበለጠ ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ሊመጣ እንደሚችል ታምኖበታል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገራችን የተከሰተውን የኑሮ ውድነትና የገንዘብ ግሽበት በዘላቂነት ለመፍታትም በነጋዴዎች ላይ የሚደረግ የአሰራር ቁጥጥርን፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅነሳን፣ ጊዜያዊ የነዳጅ ዋጋ ድጐማን፣ ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የደሞዝ ጭማሪን፣ የካፒታል በጀት ጊዜያዊ ቅነሳንና ከሁሉም በላይ የአቅርቦት መጠንን ማሳደግን ያካተቱ እርምጃዎች በበቂ ጥናትና ዝግጅት ተደግፈው ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በውይይቱ ሂደት በአሁኑ ወቅት በአገራችን ከኑሮ ውድነትና ከዋጋ ግሽበት ጋር በተያያዘ እየታየ ያለው የኢኮኖሚ ቀውስ የነፃ-ገበያ የኢኮኖሚ ስርዓት የፈጠረው ችግር ሳይሆን ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ የነፃ-ገበያ ስርዓትን በአግባቡ ለማካሄድ ካለመቻሉ ጋር በተያያዘ የተፈጠረ ቀውስ መሆኑን ጉባዔው አስምሮበት አልፏል፡፡

## 6. የውጭ ግንኙነት

የአገሪቱን ወቅታዊ የውጭ ግንኙነት በተመለከተ ጉባዔው ባደረገው አጠቃላይ ግምገማ አገሪቱ በአለም አቀፍ፣ በአህጉርና በአካባቢ ደረጃ የምትገኝበትን ሁኔታ ለመገምገም ተሞክሮል፡፡ ኢትዮጵያ በውስጧ አስተማማኝ ፖለቲካዊ መረጋጋት የማይታይበት አገር በመሆኑዋ ምክንያት በአለምአቀፍ ደረጃ ያላት ግንኙነትና ገፅታም በዚያው መጠን በርካታ ድክመቶች ያሉበት መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በውጭ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሊገኝ የሚችለውን መዋዕለ ንዋይ፣ የውጭ እርዳታና ብድርን፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትንና ቱሪዝምን በሚገባው መጠን በመሳብና በማሳደግ ረገድ የአገሪቱ ዲፕሎማሲ በርካታ ድክመቶች እንዳሉበት ታምኖበታል፡፡ በውጭ አገር የሚገኙ የአገሪቱ ኤምባሲዎች የአገሪቱን ዜጎች ጥቅምና ደህንነት በመከታተልና በማስጠበቅ ረገድ ሊሻሻል ያልቻለ ድክመት የሚታይባቸው ሲሆን ለዲፕሎማሲ ስራ በየደረጃው የሚመደቡ ሰዎች ከፍተኛ የድርጅት ፖለቲካ ወገንተኝነት የሚታይባቸው በመሆኑ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ በአግባቡ እያካሄዱ አለመሆኑ ታምኖበታል፡፡ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ደረጃ ከፍተኛ ድክመት የሚታይበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአፍሪካ አህጉር ደረጃ ያላት ዲፕሎማሲያዊ ሁኔታ ግን በተሻለ የጥንካሬ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ ኢትዮጵያ ያላት ግንኙነት የራሱ ጥንካሬና ድክመት ያለበት መሆኑ የታመነበት ሲሆን፣ አገሪቱ ከጐረቤቶቹዋ ጋር ባላት ግንኙነት ከሽብርተኝነት እንቅስቃሴ፤ ከድንበር ማካለል፤ ከድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀምና ከስደተኞች እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ያሉባትን ችግሮች ግልፅነትና ጥንቃቄ በተሞላበት አኳን መፍታት እንዳለባት ታምኖበታል፡፡ የአፍሪካን ቀንድ በመሰረተ ልማትና በንግድ የማቀራረብ ጥረትም ልዩ ትኩረት እንደሚያሻው ታምኖበታል፡፡ ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት አገር መሆኖ በወቅቱና በወደፊቱ የአገሪቱ የኢኮኖሚና የፀጥታ ህልውና ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ አሳሳቢ በመሆኑም የአገሪቱ ዲፕሎማሲ ለኢትዮጵያ የባህር በር የባለቤትነት መብት መኖር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

## 7. ምርጫ 2002 እና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የኃይል አሰላለፍ

በዕርሰ ጉዳዩ ላይ በተደረገው ውይይት በ 2002 ምርጫ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለምን ሙሉ ለሙሉ በሚባል መጠን ተሸናፊ ሆኑ? የ 2002 ምርጫ የአገሪቱን የመድብለ ፓርቲ ስርአት ከማጠናከር ይልቅ ለምን ወደኋላ የቀለበሰ ሆኖ ተጠናቀቀ? በአጠቃላይስ የ 2002 ምርጫ በአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ምን ዓይነት የኃይል አሰላለፍ ለውጥ አመጣ? ለሚሉት ጥያቄዎች ጉባዔው መልስ ሰጥቶ ለማለከፍ ሞክሮል፡፡

የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሽንፈት በተመለከተ የተለያዩ ነጥቦች በምክንያትነት ተጠቅሰዋል፡፡ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት ጎልቶ የወጣው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ 97 ማግስት የፈፀሙት ከፍተኛ ስህተት ነው፡፡ምርጫ 97 ን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ተቃዋሚዎች በምርጫ ያገኙትን ውጤት በአግባቡ ይዘውና ተጠቅመው ትግሉን አጠናክረው ከመቀጠል ይልቅ ፓርላማ ላለመግባትና አዲስ አበባ መስተዳደርን ላለመረከብ በመወሰን የወሰዱት የተሳሳተ አቋም እራሳቸውን በማዳከምና በህዝብ ዘንድ እምነት እንዲያጡ በማድረግ ለ 2002 ምርጫ ሽንፈት እንደዳረጋቸው ታምኖበታል፡፡

ለተቃዋሚዎች ሽንፈት ዋናው ምክንያት ይህ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአለፉት አምስት ዓመታት ገዢው ፓርቲ የፈፀማቸው ሁለት ተግባራት ተጨማሪ ምክንያቶች መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ ገዢው ፓርቲ በ 97 ዓ.ምቱ ምርጫ የደረሰበት ዓይነት ያልተገመተ ሽንፈት ዳግም እንዳይከሰት በመስጋት እራሱን እንደ አዲስ አጠናክሮ በመውጣት በአንድ በኩል ከአለፉት አመታት የተሻለ የልማት ስራ በመስራት የተሻለ የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት በመቻሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በህዝቡ ላይ የተለያዩ ተፅኖዎችንና ጫናዎችን ለመፍጠር የሚያስችል ድርጅታዊ አቅም በመፍጠር የ 2002 ምርጫን ለማሸነፍ መቻሉ ታምኖበታል፡፡ ገዢው ፓርቲ ከመጠን ባለፈ ስጋት ውስጥ ሆኖ በምርጫው ወቅት በህዝቡ ላይ በፈፀመው ከገደብ ያለፈ ጫና ምክንያት ምርጫውን አሣማኝ በሆነ የድምፅ ልዩነት ከማሸነፍ አልፎ የአገሪቷን የዲሞክራሲ ሂደትም ሆነ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓቱን ትርጉም በሚያሳጣ መጠን ምርጫውን እጅግ በተጋነነና በህዝብ ውስጥ ከሚታየውሰፊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ጋር በፍፁም በማይጣጣም ሁኔታ 99.6% ሊያሸንፍ እንደቻለ ታምኖበታል፡፡

ምርጫ 2002 ከዚያ በፊት ከነበረው ሁኔታ በተሻለ ገዢው ፓርቲ እንደ አንድ በምርጫ እንዳሸነፈ መንግስት የተሻለ የህዝብ እውቅና (legitimacy) ያገኘበት ወቅት ቢሆንም ኢህአዴግ በፈፀመው ከገደብ ያለፈ ጫናና ተፅእኖ ምክንያት አጠቃላዩ የምርጫ ውጤት በአገራችን የዴሞክራሲ ሂደቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና እየተጠናከረ ከመሄድ ይልቅ ወደ ኋላ እየተቀለበሰ መምጣቱን፤ አገሪቱም በአሁኑ ወቅት በአንድ አምባገነናዊ ፓርቲ ብቸኛ ቁጥጥር ስር በመውደቅ የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን በአግባቡ ለማስተናገድ እንዳልቻለች ያረጋገጠ ሂደት ሆኖ እንዳለፈ ታምኖበታል፡፡

ከፖለቲካ ድርጅቶች የኃይል አሰላለፍ አንፃር ምርጫ 2002 ኢህአዴግን በአገሪቱ ብቸኛ አምባገነናዊ ኃይል ሆኖ እንዲወጣ ያደረገ ሲሆን በአንፃሩ ተቃዋሚዎችን የበለጠ የተዳከሙና ለህዝቡ የለውጥ ተስፋ የማይሰጡ ኃይሎች እንዲሆኑ እንዳደረጋቸው ታምኖበታል፡፡ ህዝቡም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንደ አንድ አማራጭ ኃይል ያለማየት ተስፋ መቁረጥ ውስጥ በመግባትና ኢህአዴግን እንደ አንድ በውድም ሆነ በግድ አገሪቱን እየገዛ ወደፊት ከመቀጠል የማይመለስ ድርጅት አድርጐ በማዬት በትግሉ ሂደት የመሳተፍ ፍላጐቱ እየቀዘቀዘ መምጣቱ ታምኖበታል፡፡ ይህ ሁኔታ ተለውጦ የትግሉ ሂደት እንደገና እንዲጠናከርም በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች በ 2002 ምርጫ የደረሰባቸውን ሽንፈት በሃቅና በድፍረት በመገምገም ከድክመቶቻቸውና ከስህተቶቻቸው ተምረው አዲስ ስልትና ስትራቴጂ ቀይሰው መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅባቸው፤ ህዝቡም በጊዜያዊ ሁኔታ ተደናግጦ ተስፋ መቁረጥ ዘላቂ መፍትሄ እንደማይሆን በግልፅ ተገንዝቦ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደገና ተጠናክረው ለመውጣት የሚያስችላቸውን ሁለንተናዊ እገዛ ማድረግ እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

ምርጫ 2002 በአገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሂደትና በአጠቃላይ በተቃዋሚው ጐራ አስከትሎት ያለፈው ጉዳት ከባድ ቢሆንም ከስህተቱ ለመማር ዝግጁ ለሆነ አካል ሂደቱ ከፍተኛ ትምህርት ሊቀሰምበት የሚችል ሂደት እንደነበር ታምኖበታል፡፡ ኢዴፓ ተቃዋሚ ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን በ 2002 ምርጫ በተቃዋሚው ጐራ የደረሰውን ጉዳት በቀጥታ የሚጋራ ቢሆንም የምርጫው ሂደት ለኢዴፓ የተለየ ትርጉምና ፋይዳ እንደነበረው ታምኖበታል፡፡ ኢዴፓ ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ የተካሄደበትን ያሉባልታ ዘመቻ በማክሸፍ በምርጫ ዘመቻው ወቅት ከሌሎች ፓርቲዎች የተሻለ ዝርዝር ማንፌስቶ ያቀረበ፣በምርጫው ወቅት በተካሄዱ የክርክር መድረኮችም የሃሳብ አሸናፊነቱን ያሳዩ፣ በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች ባካሄዳቸው ህዝባዊ ስብሰባዎችም የማይናቅ የህዝብ ድጋፍ ያለው ፓርቲ

መሆኑን ያሣዬና በመጨረሻ በምርጫው በተገኘው የህዝብ ድምፅም በአገሪቱ ከሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ በተናጠል ፓርቲነት ሲሰላ የተሻለ የህዝብ ድምፅ ያገኘ ፓርቲ መሆኑን ያረጋገጠበት ሂደት መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ይህ ሁኔታም ለኢዴፓ የወደፊት ጥንካሬ እንደ አንድ በጐ አጋጣሚና ዕድል የሚቆጠር መሆኑ ታምኖበታል፡፡

## 8. የአገሪቱ የፖለቲካ ተዋናኞች /political Actors/ የሚገኙበት ሁኔታ

በአገሪቱ ፖለቲካ የጎላ ሚና ያላቸውን የፖለቲካ ተዋናዮች በተመለከተ ጉባዔው ባደረገው ግምገማ የገዢውን ፓርቲ፣ የተቃዋሚ ፓርዎችን፣ የዴሞክራሲ ተቋማትን፣ የህዝቡንና በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ሚና ለመገምገም ተሞክሮል፡፡

በአገራችን የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንፃር ሲመዘኑ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ሁሉም (ኢዴፓን ጨምሮ) በደካማ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑ የታመነበት ሲሆን ከአገራዊ አጀንዳዎች ጥንካሬና ጥራት አንፃር ግን በአገራችን የሚገኙ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲዎች የተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ታምኖበታል፡፡ ነገርግን አብዛኛዎቹ ህብረ-ብሄራዊ ፓርቲዎች በወረቀት ደረጃ ይዘነዋል የሚሉትን አስተሳሰብና አገራዊ አጀንዳ ወጥና ግልፅ በሆነ ሁኔታ የማራመድና የመተንተን ድክመት ስለሚታይባቸው ከአገራዊ አጀንዳ አንፃር ያላቸው አንፃራዊ ጥንካሬም ጥያቄ ውስጥ እየወደቀ የመጣ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በእኩል የውድድር ሜዳ ተወዳድሮ ያገኘው ባይሆንም ከድርጅት ጥንካሬ አንፃር ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ሲነፃፀር በጠንካራ ድርጅታዊ አቋም ላይ እንደሚገኝ የታመነበት ሲሆን ከአገራዊ አጀንዳዎች ጥንካሬ አንፃር ግን ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ በከፍተኛ ድክመት ውስጥ የሚገኝና በግልፅ ማንነቱ የሚታወቅ ርዕዮተ ዓለማዊ አቅጣጫ ማራመድ የተቸገረና ግራ የተጋባ ድርጅት መሆኑ ታምኖበታል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ (በተለይም የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርገው ህብረተሰብ) ከዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አንፃር የሚገኝበትን ደረጃ ለመገምገም በተደረገው ሙከራም ህዝቡ በተለያየ አገራዊ ጉዳዮች በርካታ የራሱ የሆኑ ጠንካራ ጐኖች ያሉት ህዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያው መጠን ከዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ተሳትፎ አንፃርግን ሊሻሻሉ የሚገባቸው በርካታ ድክመቶች ያሉበት መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ሕዝቡ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚደረገውን ትግል በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በጊዜና በእውቀት ተሳትፎ እያደረገ ከማጠናከር ይልቅ እራሱን ከሂደቱ ገለል በማድረግ በሌሎች ተሳትፎና መስዋዕትነት ለውጥ እንዲመጣ የመፈለግ፣ የሚፈለገው ለውጥ በቀላሉና በአጭር ጊዜ መምጣት ሳይችል ሲቀርም በቀላሉ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ የመግባትና እራሱን ከሂደቱ የማራቅ አዝማሚያ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚታዩ ድክመቶች ዋና ዋናዎቹ መሆናቸው ታምኖበታል፡፡ እነዚህ መፍትሄ የሚያሻቸው ድክመቶች በህብረተሰቡ ዙሪያ መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ 97 ዓ.ምቱ ምርጫ በኋላ ህዝቡ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚመዝንበት መንገድ በሂደት አዝጋሚ የሆነ መሻሻል እየታየበት መምጣቱ ታምኖበታል፡፡ በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በፖለቲካ ትግሉ ዙሪያ ያላቸው ተሳትፎ በሂደት አንዳንድ በጐ አቅጣጫዎች እታዩበት ቢሆንም አሁንም በአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት የሚጠበቀውን ያህል ገንቢ ሚና ለመጫዎት ያላስቻሉት በርካታ ድክመቶች በዙሪያ እንደሚገኙ ታምኖበታል፡፡

ከዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተቋማት ሚና በተመለከተ ጉባዔው ባደረገው ግምገማ ነጻ፣ ገለልተኛና ጠንካራ ተቋሟት በሌሉበት ሁኔታ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት መገንባት እንደማይቻል አምኖበታል፡፡ በአገራችን በአሁኑ ወቅት ከመልካም አስተዳደር፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ ከሰብዓዊ መብት፣ ከሰላምና ከአገር ደህንነት ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ነጻ፣ ገለልተኛና ጠንካራ ሆነው አለመገኘታቸው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱን ከባድና ውስብስብ እንዳደረገው ታምኖበታል፡፡ ይህ አገራዊ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ያገኝ ዘንድም ከማንም በላይ መንግሥትና ገዥው ፓርቲ ተቋማትን ሌሎችን ለማጥቃትና እራስን ከሌሎች ጥቃት ለመከላከለ በመሳሪያነት ከመጠቀም ይልቅ ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ተደራጅተው አገርንና ሕዝብን እንዲያለግሉ መደረግ እንዳለበት፣ ተቃዋሚዎችና ሕዝቡም ለነጻና ገለልተኛ ተቋሟት መኖር ልዩ ትኩረት ሰጥተው መታገል እንዳለባቸው ታምኖበታል፡፡

## **9.** የፖለቲካ ፓርቲዎች የትግል ስልት

የፖለቲካ ፓርቲዎች የትግል ስልትን በተመለከተ ጉባዔው ባደረገው ግምገማ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በዋናነት ሶስት አይነት ማለትም-ሰላማዊ ትግል፣ የትጥቅ ትግልና ሁለገብ ትግል የሚባሉ ስልቶች በተለያዩ ፓርቲዎች

ሲቀነቀኑ የሚታዩ ሲሆን ከእነዚህ አማራጭ ስልቶች ውስጥ የኢዴፓ ምርጫ ሰላማዊ ትግል ብቻ ሆኖ መቀጠል እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ ከምርጫ 97 በኋላ የሰላማዊ ትግሉ ሂደት የመዳከም አዝማሚያ ያሳየ ቢሆንም ድክመቱ ሊከሰት የቻለው ሰላማዊ ትግል በአገራችን አዋጭ ስልት ስላልሆነ ሳይሆን ሰላማዊ ትግል እናራምዳለን የምንለው ድርጅቶች ሠላማዊ ትግልን በአግባቡ ለማካሄድ የሚያስችል ድርጅታዊ ጥንካሬና ህዝባዊ እንቅስቃሴ መፍጠር ባለመቻላችን የተከሰተ ድክመት መሆኑ ታምኖበታል፡፡ አንድ ህዝብ መብቱን በብቃት ከተገነዘበና ለመብቱ መከበር የሚጠበቅበትን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ከሆነ በሰላማዊ ትግል ምን ያህል በአጭር ጊዜ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል የወቅቱ የቱኒዚያና የግብፅ ሁኔታ ያረጋገጠ መሆኑን በማውሳትም የኢትዮጵያ ህዝብ ከግጭትና ከጦርነት በፀዳ መንገድ በሰላማዊ ትግል ማዕቀፍ ውስጥ የሚታወቁትን ስልቶች በብቃት መጠቀም ከቻለ ትግሉን በአጭር ጊዜ ለአሸናፊነት ማብቃት እንደሚቻል ታምኖበታል፡፡ ይህ እውን እንዲሆንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሰላማዊ ትግል ፍፁም ታማኝ በመሆን ህዝቡን በዙሪያቸው የማደራጀትና የማብቃት ስራ መስራት እንደሚጠብቅባቸው ታምኖበታል፡፡

ከፖለቲካ ፓርቲዎች የትግል ስልት ጋር በተያያዘ በፓርቲዎች አብሮ የመስራት ጥያቄ ዙሪያ በተደረገው ውይይት ህብረ-ብሄራዊ አደረጃጀትና ተቀራራቢ የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸው ድርጅቶች በህብረት አብረው ከመስራትም አልፎ ወደ ውህደትና አንድነት መምጣት ቢችሉ ትግሉን በፍጥነት በማጠናከር ረገድ ጠቃሚ መሆኑ በመርህ ደረጃ ታምኖበታል፡፡ ነገር ግን በአንድነት መስራት የሚፈልጉ ፓርቲዎች ተመሳሳይ አደረጃጀትና ተቀራራቢ የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸው ከመሆኑ አስፈላጊነት በተጨማሪ አብረው ለመስራትም ሆነ ወደ አንድነት ለመምጣት የሚፈልጉ ፓርቲዎች በቅድሚያ ውስጣዊ የዴሞክራሲ ባህል ያላቸው፣ ከግለሰብ ስብስብነት ያለፈ ድርጅታዊ ጥንካሬ የፈጠሩና ለሌሎች ፓርቲዎች ተገቢውን አክብሮትና እውቅና መስጠት የቻሉ መሆን እንዳለባቸው ታምኖበታል፡፡

## 10. የኢዴፓ የወደፊት አጠቃላይ አቅጣጫ

የኢዴፓን የወደፊት አጠቃላይ አቅጣጫ በተመለከተ ጉባዔው ባደረገው ውይይት-ኢዴፓ በአንድ በኩል ከዚህ በላይ በግምገማ የተደረሰባቸውን አቋሞች መሰረት አድርጐ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ፖለቲካ እየፈጠረው የሚገኘውን የሃሳብ የበላይነት የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንፃር ያሉበትን መሰረታዊ ድክመቶች በመፍታት በየደረጃው የሚገኙ ድርጅታዊ መዋቅሮችን ማጠናከርና በህዝቡ ውስጥ በስፋት መንቀሳቀስ እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ትኩረት አንፃርም የዛሬ ሁለት ዓመት በአዲስ አበባ ከተማ በሚካሄደው የክልል ምክር ቤት ምርጫ ኢዴፓ ምርጫውን አሸንፎ አዲስ አበባ መስተዳድርን ለመረከብ የሚያስችለውን ሁለንተናዊ ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

የኢዴፓ 5 ኛ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባኤ
መጋቢት 11 ቀን 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ